# የልደታ ክፍለ ከተማ ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወር የዕቅድ አፈጻፀም ሪፖርት

**ታህሳስ/2017ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## ክፍል-አንድ

## 1. መግቢያ

በልደታ ክ/ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በከተማ አስተዳደሩ የተሰጠውን ተልዕኮ በማሰካት ረገድ ባለፉት ዓመታት በከተማዋ ስር ሰዶ የቆየውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በዘላቂነት በመቅረፍ ፈጣንና ፍትሃዊ ልማት ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል አደረጃጀታዊ መዋቅር በአዲስ መልክ ተቋቁሞ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ስለሆነም ዘርፉ የተቋቋመበትን ዓላማና የተሰጠውን ተልዕኮ እውን ለማድረግ፤ በየጊዜው የአሰራር ዘዴውን እየፈተሸ ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል አደረጃጀት፣አሰራር እንዲሁም በከተማዉ የሚሰጠውን አግልግሎት በግልጽነት፣በተጠያቂነት እና በፍትሃዊነት መርህ መሠረት እንዲያገኝ ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ በመሆኑ፤ህብረተሰቡ በሚኖርበት ብሎክ ያሉትን ችግሮች እንዲለዩ በማድረግና በመፍታት የመንግስት መዋቅሩን በመደገፍ እንዲሁም ችግሮችን በጋራ እንዲፈታ ነጻና ግልጽ በሆነ መልኩ ማሳተፍ ለሁለተናዊ ለውጥ ወሳኝ በመሆኑ መንግስት ሕዝቡን በየደረጃው በማሳተፍ፤ የህዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ እንዳለበት በመደንገጉና ይህን ተግባራዊ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ነዋሪዎች ስለከተማዉ የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ሀሳብና ጥያቄ የማቅረብ መብታቸዉን እንዲጠቀሙ የብሎክ መዋቅሩን ከማደራጀትና የተሰሩ የሰላምና ፀጥታ ፣የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፣ የልማት እና የአገልግሎት፣አሰጣጥ ስራዎች ላይ ያለዉን የተግባር እንቅስቃሴ የሚያሳይ የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወር የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2 ራዕይ

በ2022 ዓ.ም የለማ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በጎ ፈቃድን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ተፈጥሮ ማየት፡፡

## 1.3. ተልዕኮ

በከተማው አስተዳደሩ ብሎክን ማዕከል ያደረገ የአግልግሎት አሰጣጥ፣ የመሠረተ ልማት፣ የፀጥታ ችግሮችን እና የበጎ ፈቃድ ተግባራት ፍላጎትን በመለየት የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት ችግሮችን ከምንጫቸው እንዲፈቱ በማድረግ የህብረተሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ፡፡

## 1.4. ዕሴቶች

1. **አሳታፊነት**፡ ህብረተሰቡ በልማት፣በፀጥታና በአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም በበጎ ፈቃድ ተግባራት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ፤
2. **ሰብአዊነት**፡ በራስ ተነሳሽነነትና ፍላጎት ለሌላው ማህበረሰብ በጎ ተግባራትን መፈጸም፤
3. **ፍትሃዊነት**፡ በብሎክ የሚገኙ ነዋሪዎች የሠላሙና የልማቱ በእኩልነትና በፍትሀዊነት ተቋዳሽ እንዲሆኑ ማስቻል እንዲሁም የበጎ ፈቃድ ማህበራትን በማስተባበር ፍትሀዊ አሰራርን ስርዓት መዘርጋት፤
4. **ተጠያቂነት**፡ ነዋሪው ህብረተሰብ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚታዩትን ጉዳዮች የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፤
5. **በዕውቀትና በእምነት መሥራት**፡ መንግስት የሚሠጣቸው አገልግሎቶች ህብረተሰቡ እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
6. **ለለውጥ ዝግጁነት**፡ አገልግሎት ሰጭውም ሆነ ተቀባዩ አካል ለለውጥ ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ
7. **ጥራትና ወጪ ቆጣቢነት**፡ በህብረተሰቡ የሚሰሩ የልማት ተግባሮች ጥራታቸውን የጠበቁና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆኑ ማድረግ፤
8. **ችግር ፈቺነት**፡ መንግስትና ነዋሪው ህብረተሰብ ለሚፈጠሩት ችግሮች መፍትሔ አምጪ እንዲሆኑ ማድረግ፤

## ክፍል ሁለት

2. የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወር ቁልፍ ተግባር፤ አላማ፣ ግቦች እና ተግባራት

## የአስተዳደር ዘርፍ ሥራዎች ዕቅድ ክንውን

### ግብ 1፡- ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የህብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት

### ዓላማ1፡- የዕቅድ አዘገጃጀት እና የትግበራ ሪፖርት ተደራሽነት አሰራር ማሻሻል

ተግባር1፡- 1 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ መሪ ዕቅድ እና የተከለሰ ዕቅድ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 2፡- ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ 9 ሪፖርት ሰነድ ለማዘጋጅት ታቅዶ 9 ሪፖርት መዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 3፡- 1 ወቅቱን የጠበቀ መሪ ዕቅድ እና የተክለሰ ዕቅድ ሰነድ ለመላክ ታቅዶ 1 ጊዜ ተዘጋጅቶ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 4፡- ወቅቱን የጠበቀ 9 ሪፖርት ለመላክ ታቀዶ 9 ሪፖርት ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 5፡- በዕቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፀምና ግምገማ ዙሪያ ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ በየደረጃው 2 መድረክ ለመፍጠር ታቅዶ 2 ጊዜ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 6፡- በዕቅድ ክለሳ፣ አፈፃፀምና ግምገማ መድረክ ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ በየደረጃው በድምሩ 700 አመራር፣ ሰራተኞች፣ ባለድርሻ አካላትና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 750 ማሳተፍ ተችሏል ፡፡ አፈጻጸሙን 100% □□□ ማድረስ ተችላል፡፡

### ዓላማ2፡- የተቋም እቅድ ጥራትና አፈፃፀም አሰራርን ውጤታማነትን ማሻሻል

ተግባር 1፡- የጽ/ቤቱ ዕቅድ 2 ጊዜ ከዘርፍ ዕቅድ እንዲሁም በተዋረድ ከሚገኙ ጽ/ቤቶች ዕቅድ ጋር ለማናበብና ለማጣጣም ታቅዶ 2 ጊዜ ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 2፡- በየሩብ ዓመት 2 ጊዜ አፈጻጸም ከቡድኖችና ከወረዳ ዘርፍ ጽ/ቤቶች ጋር በጋራ ስራ መገምገምና ዉጤታማ ለማድረግ ታቅዶ 2 ጊዜ ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር3፡- 2 ጊዜ በየደረጃዉ የክትትልና ድጋፍ ስራ ለማከናወን ታቅዶ 2 ጊዜ ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

### ዓላማ3፡- የተቋም በጎ አድራጎት እና ኢንሸቲቪ ሥራዎችን ማጎልበት

ተግባር 1፡ 200 የጽ/ቤቱን ሠራተኞች እና አጋር አካላትን በማሳተፍ የአረንጓዴ አሻራ ተግባራት ተሳታፊ በማድረግ 900 ችግኞችን መትከልና የተተከሉትን ችግኞች እንዲንከባከቡ ለማድረግ ታቅዶ 350 ተሳትፎ በማድረግ 900 ችግኞችን መትከልና የተተከሉትን ችግኞች መንከባከብ ተችሏል። አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል።

ተግባር 2፡- ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በጽ/ቤቱ 1 ቤት በማደስ ድጋፍ ለማድረግ በታቀደው መሰረት 1 ተከናውኗል። አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር 3፡- 1 ወላጅ አልባ ህፃን ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 1 ድጋፍ ማድረግ ተችሏል። አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር4፡- ለ33 የጽ/ቤቱ ዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ ሠራተኞች ማዕድ ለማጋራት ታቅዶ 40 ሰራተኞች ማዕድ ማጋራት ተችሏል። አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል።

**ዓላማ4፡- በተቋማት የጸረ ሙስና ትግል ማጎልበት፡፡**

ተግባር1፡-በተቋሙ የጸረ ሙስና 1 እቅድ አዘጋጅቶ ከሰራተኛው ጋር ተግባቦት በመፍጠር የሙያ ስነ-ምግባር ግንባታ ለማድረግ ታቅዶ 1 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር2፡-ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል 1 የማክሰሚያ ስትራቴጂና ተጋላጭነትን ለይቶ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ 1 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር3፡- በተቋሙ ብልሹ ተግባራትን እና አደጋዎችን በማጋለጥ ተጠያቂነት ለማስፈን 100% ተጨባጭ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ 100% እርምጃ ተወስዷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

**ዓላማ5፡- ተቋሙ የሚገለገልባቸውን የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ግዥ በመፈፀም 100%**

**ጥቅም ላይ ማዋል**

ተግባር 1፡- ከየሥራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን፣ መጠመርና የግዥ ዕቅድ 1 ጊዜ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 ጊዜ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር 2፡- ለበጀት አጠቃቀም ሲባል ወቅታዊ የገበያ ጥናት በዓመት 1 ጊዜ ለማካሄድ ታቅዶ 1 ጊዜ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር 3፡- በተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ተጠቅመን 1 ጊዜ ግልጽ ጨረታ በማውጣት ግዥዎችን ለመፈፀም 1 ጊዜ ተከናውኗል፡፡ የዕቅዱን 100% ማከናወን ተችላል።

ተግባር 4፡- በማዕቀፍ የሚገዙትን ዕቃዎች 100% ፍላጎት በመለየትና በማሳወቅ የግዥ ሂደቱን በመከታተል ከአቅራቢ ድርጅት ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር 5፡- የንብረት ስራ አመራር በማዘመን የገቢና ወጪ ስርዓት 100% ለማከናወን ታቅዶ 100% ማከናውን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር 6፡- የተሽከርካሪ ስምሪት፣ ጥገናና ሰርቪስ የአሰራር ስርዕቱን ጠብቆ 100% እንዲከናወን ለማድረግ ታቅዶ 100% ማከናውን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል።

ተግባር 7፡- በውል የሚፈጸሙ ስራዎችን 100% ለማስተዳደር ታቅዶ 100 %ማከናውን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

### ዓላማ6፡- የበጀት አጠቃቀም አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

ተግባር1፡- ለበጀት ዓመቱ የተመደበው በጀት ለሁሉም የሥራ ክፍሎች በመደልደል በአግባቡ 100% ሥራ ላይ ለማዋል ታቅዶ 100% ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር2፡- ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት 100% መቀነስና በተገኙ ግኝቶች ላይ 100% ተጨባጭ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

### ዓላማ7፡- የሴቶች ማህበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል፡፡

ተግባር1፡- የህጻናት ማቆያ አገልግሎት በመስጠት 100% ሴት ሰራተኛ ተጠቃሚ ለማድረግ ተቅዶ 100% ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር2፡- ለ35 ሴት ሰራተኞች 100% ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 50 ሴት ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር3፡- ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ቦታን በመፍጠር 100% እርካታ ለማፍጠር ታቅዶ 100% ማድረስ ተችሏል ፤አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

## ዓላማ8፡- የመልካም አስተደደር ችግሮችን በመፍታት የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፡፡

ተግባር1፡በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች 100% መለየትና እንዲፈቱ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ100% መፍታት ተችሏል፤

ተግባር2፡- ለሚቀርቡ ቅሬታዎች 100%ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 100% ምላሽ መስጠት ተችሏል፤፤

ተግባር3፡- ስታንዳርዱን ጠብቆ 100% አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 100% ምላሽ መስጠት ተችሏል፤

ተግባር 4፡- መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ 85% ለማድረስ ታቅዶ 84.2% ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር 5፡- በ6 ወር ውስጥ 1 ጊዜ የምዘና ስራ ለማከናወን ታቅዶ 1 ጊዜ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

## ግብ2 ፡- የመረጃ ጥራትና ተደራሽነትን በማስፋት የህብረተሰቡን የመረጃ ፍላጎት ማርካትና የተሟላ መረጃ ያለው ህብረተሰብ መፍጠር፡፡

### ዓላማ1፡- የመረጃ ሽፋን ጥራትና ተደራሽነትን ማድረስ፡፡

ተግባር 1፡- በዓይነት 2 ልዩ ልዩ የህትመት ውጤቶችን ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ታቅዶ 2 ማዘጋጀትና ማሰራጨት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 2፡- በቁጥር 6 ዜናዎችን በማዘጋጀት ለማሰራጨት ታቅዶ 9 ዜናዎች ተዘጋጅተው ተሰራጭተዋል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 3፡- 19 የማህበራዊ ሚዲያ ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 21 ማከናወን ተችሏል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

## ዓላማ 2፡- የቀረፃ፣ ቅንብርና ዶክመንቴሽን ስራን ማሳደግ፡፡

ተግባር 1፡- 41 ፎቶዎችንና የቪዲዮዎች ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ 50 ፎቶዎችንና የቪዲዮ ማከናወን ተችሏል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 2፡- 1 የምስልና ድምጽ ስራዎችን በውስጥና በውጪ አቅም ማቀናበርና ለማሰራጨት ታቅዶ 1 ተሰራጭቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

# ግብ 3፡- በጽ/ቤቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት እንዲፈጠር ፤ ግልፅኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያስችሉ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ማጠናከር

## ዓላማ 1፡- የህዝብ ግንኙነት መድረኮችን ወደ 16 ማሳደግ፡፡

ተግባር 1፡- 1 የሁነት መድረኮችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 2 ሁነት መድረኮችን ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 2፡- 1 የፓናል ውይይት ዝግጅት ለማከናወን ታቅዶ 2 ተከናውኗል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 3፡- 1 የአዳራሽ ፎቶ አውደ ርዕይ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 ተዘጋጅቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 4፡- 1 ጊዜ ከአቻ ክፍለ ከተሞች ጋር የጉብኝት መርሐ ግብሮችን ለማከናወን ታቅዶ 1 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

## ግብ 4፡ ባለ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮቸን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል

ተግባር 1፡- በተለያዩ የማህበራዊ ቀውስ የተፈናቀሉ 50 የህብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ ለማጋራት ታቅዶ 60 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡
ተግባር 2፡- በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ የሚገኙ 550 ሴቶች በማዕድ ማጋራት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 720 ሴቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡
ተግባር 3፡- በዝቀተኛ የኑሮ ደረጃ ስር ያሉ በኤች አይ ቪ ወላጆቻቸው ያጡ 50 ህጻናት ማህበራዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 300 ህጻናት ማህበራዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡
ተግባር 4፡- በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ስር ያሉ 7 አካል ጉዳተኞች ማህበራዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 40 ማህበራዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡
ተግባር 5፡- በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ስር ያሉ 10 ኤች አይ ቪ ቫይረስ ተሸካሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 12 ማህበራዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

## የህብረተሰብ ተሳትፎ ዘርፍ በ6 ወር የተሰሩ ሥራዎች (ዕቅድ ክንውን)

## ግብ4:- አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በመጠቀም ለማህበራዊና ለልማት የሚውል ሃብት ማሳደግ፤

### ዓላማ1:- ከህብረተሰቡና ከለጋሽ አካላት ለመሰረተ ልማትና ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል ሃብት 100 % መሰብሰብ፤

ተግባር1:- ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ሀብት የማሰባሰብ ስራ ለመስራት 2 ታቅዶ 2 ፕሮጀክት የመቅረጽ ስራ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር2:- ከህብረተሰቡ ለአካባቢ መሰረተ ልማት በጥሬ ገንዘብ 14,400,000.00 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 7,927,980.00 ብር መሰብሰበ ተችሏል፡፡ የእቅዱን 55 % ማከናወን ተችሏል፡፡

ተግባር3:- ከህብረተሰቡ ለአካባቢ መሰረተ ልማት በዓይነት/ቁሳቁስ 12,687,501.00 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 27,856,500 ብር ሀብት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር4:- ከህብረተሰቡ ለአካባቢ መሰረተ ልማት በጉልበት የሚደረግ አስተዋጽኦ በገንዘብ 1,500,000.00 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 3,343,050 ብር ሀብት መሰብሰብ ተችሏል ፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

ተግባር 5:- ለመሰረተ ልማት ተግባር በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የብሎክ ነዋሪዎች ድጋፍ የሚውል ሀብት ለመሰብሰብ 2,500,000 ታቅዶ 2,850,000 ብር ሀብት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

### ዓላማ2:-የፋይናንስ ደንብና መመሪያ የተከተሉ የገቢና የወጪ አፈፃፀም100% መፈፀም፤

ተግባር1:-ለመሠረተ ልማት እና ለቅጥር ጥበቃ አንድ ጊዜ የገቢና የወጪ ሃብት 100% ኦዲት ለማስደረግ ታቅዶ 100 % ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

## ግብ5:- የአሰራር ጥናት ውጤታማነትን ማሳደግ እና የአቅም ማጎልበት ሥራ መሥራት፡፡

### ዓላማ1:-በቅንጅት ከአጋር አካላት ጋር ውጤታማ ጥናት ማድረግ፤

ተግባር 1:-በህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ በቅንጅት ከአጋር አካላት ጋር 1 ውጤታማ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 1 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡

### ዓላማ3:- ለብሎክ ካውንስል አመራሮች፤ለበጎ ፈቃድ ማህበራት፤ለቅጥር ጥበቃዎች፤ለዘርፍ አመራሮች እና ባለሙያዎች እንዲሁም ለባለድርሻ አካላት የአቅም ማጎልበት ሥልጠና መስጠት

ተግባር1:- ለ1680 ለብሎክ ካውንስል አመራሮች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1730 ካውንስሎችና አመራሮች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ 100% በላይ ተከናውኗል፡፡

ተግባር2:- ለበጎ ፈቃድ ማህበራት ሥልጠና ለመስጠት 508 ታቅዶ 565 ማህበራት ስልጠና

ተሰጥቷል፡፡ 100% በላይ ተከናውኗል፡፡

ተግባር3፡- ለቅጥር ጥበቃዎች ሥልጠና ለመስጠት 100 ታቅዶ 200 ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ የዕቅዱን 100% በላይ ተከናውኗል፡፡
ተግባር4፡- በድግግሞሽ ለዘርፍ አመራሮች እና ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት 200 ታቅዶ ለ265 ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የዕቅዱን 100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡
ተግባር 5፡- ለባለድርሻ አካላት ሥልጠና ለመስጠት ለ 62 ታቅዶ ለ 62 ለባለድርሻ አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የዕቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

## ግብ6፡- ብሎኮችን መልሶ ማደራጀት፡፡

### ዓላማ1፡- ብሎኮችን መልሶ ማደራጀት፤

ተግባር1፡- 317 ብሎኮችን ማጠናከርና ለመደገፍ በታቀደው መሰረት መልሶ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

### ዓላማ2፡- መልሰው የተደራጁ ብሎኮችን ለህብረተሰቡ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ የማጠናከር ሥራ መስራት፤

ተግባር1፡- በቋሚ የግንኙነት ጊዜ የካውንስል አደረጃጀቶች 42 ጊዜ ውይይት እንዲያደርጉ ለማስቻል ታቅዶ 42 ጊዜ ውይይት አድርገዋል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር3፡- በየወረዳው በድምሩ 40 ብሎኮችን ሞዴል ለማድረግ ታቅዶ 64 ሞዴል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግብ7፡- በመሰረተ ልማት ስራዎች የኅበረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ ፡፡**
**ዓላማ1፡- ከህብረተሰቡ በተሰበሰበ ሀብት የነዋሪውን የመሠረተ ልማት ፍላጎት 90% ማሟላት፤**
ተግባር1፡- በህብረተሰብ ተሳትፎ የተለዩ 12 የመሰረተ ልማት ፈላጎት ስራዎችን በ12 ወረዳዎች መለየት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር2፡- የመሠረተ ልማት የግንባታ ዲዛይኖችን ማዘጋጀት ተችሏል፤

ተግባር3፡- የመሰረተ ልማት የግንባታ የጨረታና ውለታ አስተዳደር 100% ለማዘጋጀት ታቅዶ ጨረታ ውለታ አልቆ ወደ ስራ መግባት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር4፡- ሰብቤዝ ለመስራት 1.7015 ኪ.ሜ ታቅዶ 2.053 ኪ.ሜ ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 5፡-ኮብልስቶን ጥገና ለመስራት 4.106 ኪ.ሜ ታቅዶ 1.19 ኪ.ሜ ተከናወኗል፡፡ የዕቅዱን 29% ማከናወን ተችሏል፡፡

ተግባር 6፡- አነስተኛ ድልድይ ለመስራት በ6 ወር ውስጥ እቅድ አልተያዘም የተከናወነም የለም፡፡

ተግባር 7፡- ቱቦ ቀበራ ለመስራት 1.7135 ኪ.ሜ ታቅዶ 1.768 ኪ.ሜ ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 8፡- ቱቦ ጥገና ለመስራት 1.3705 ኪ.ሜ ታቅዶ 1.565 ኪ.ሜ ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 9፡- ካልቨርት ለመስራት 4 ታቅዶ 7 ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር 10፡- ኮሚዩኒቲ ፖሊስ ግንባታ ለመስራት 1 ታቅዶ 6 ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 11፡- የውስጥ ለውስጥ የመንገድ መብራት ለመስራት 0.387 ኪ.ሜ ታቅዶ 1.35 ኪ.ሜ መስራት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 12፡- የጋራ መጸዳጃ ቤቶች ለመስራት 3 ታቅዶ 10 ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 13፡-ዲች ስራ ለመስራት 0.9005 ኪሜ ታቅዶ 0.685 ኪ.ሜ ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙን 76% ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 14፡- ጠጠር ገረጋንቲ ለመስራተ ለመስራት 0.0095 ኪሜ ታቅዶ 0.415 ኪ.ሜ መስራት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር 15፡- የቴራዞ መንገድ ግንባታ ስራ ለማከናወን 0.2415 ኪ.ሜ ታቅዶ 0.24 ኪ.ሜ መስራት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችላል፡፡
ተግባር 16፡- የድጋፍ ግንብ ስራ ለማከናወን 0.522 ኪ.ሜ ታቅዶ 0.5 ኪ.ሜ በመስራት አፈጻፀሙን 96% ማከናወን ተችሏል፡፡

ተግባር17፡- 12 የተጠናቀቁ የመሰረተ ልማት ስራዎች ለመስራት ታቅዶ 12 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

### ዓላማ2፡- በሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ተግባራት ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ፤

ተግባር1፡- ለ139 ዜጎች በጊዜያዊነት የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 212 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር2፡- 7,129,384.38 ብር የሚሆን የገበያ ትስስር ለማህበራት ለመፍጠር ታቅዶ 49,190,307 ብር የገበያ ትስስር ተፈጥሯል ፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

## ግብ8፡- ህብረተሰቡን በብሎክ በማደራጀት የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ ማስፈን

### ዓላማ1፡- የብሎክ ነዋሪዎች በሰላም እሴት ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ፤

ተግባር1፡- የብሎክ ነዋሪዎች በህገ ወጥነት መከላከል፤በሰላም ማስፈንና በወንጀል መከላከል ዙሪያ ውይይት እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር 48,236 ታቅዶ 79,046 ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡
ተግባር2.፡- 24,000 የብሎክ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን በየተራ እንዲጠብቁ ታቅዶ 53,963 ነዋሪዎች ጥበቃ አድርገዋል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

### ዓላማ2፡- ለደህንነት ስጋት የሆኑ ቦታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መለየትና ማስተካከያ ማድረግ

ተግባር1፡- ስጋት የሆኑ ቦታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት /ከፖሊስ ኮሚሽን ፤ከሰላምና ፀጥታ እና ከደንብ ማስከበር ጋር በጋራ በመሆን ለመለየት 22 ታቅዶ 71 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

### ዓላማ3፡- የብሎክ ነዋሪው የቅጥር ጥበቃ በመቅጠር አካባቢውን ማስጠበቅ

ተግባር1:- 53 ቅጥር ጥበቃ ለማስቀጠር ታቅዶ 85 ቅጥር በመፈፀም አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

## ዓላማ4፡-ነዋሪዎች በአካባቢያቸው በውስጥ ለውስጥ መንገዶች 9,500 የምሽትአምፖልእንዲያወጡ ማድረግ፤

ተግባር 1:- በመብራት ተደራሽ ያልሆኑ የውስጥ ለወስጥ መንገዶች ህብረተሰቡ  አምፖል እንዲወጣ 4750 ታቅዶ 4816 አምፖል ማውጣት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

## ዓላማ 5፡- ብሎኮችን ከኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሴንተሪ ጋር ማስተሳሰር

ተግባር1:- በብሎክ ደረጃ የተሰሩትን የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሲንተሮችን 100% ቆጠራ ለማድረግ ታቅዶ 100% ቆጠራ ማድረግ ተችሏል፡፡
ተግባር2፡- 317 ብሎኮችን ከኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሴንተሪ ጋር 100% እንዲተሳሰሩ ለማድረግ ታቅዶ 100% ማስተሳሰር ተችሏል፡

## ዓላማ6፡- የብሎክ አደረጃጀትን በመጠቀም ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥን ማሳደግ

ተግባር1:- ከብሎክ እስከ ከከተማ የ24 ሰአት መረጃ ልውውጥ ለማድረግ 26 ታቅዶ 30 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

## ዓላማ7፡- በብሎክ አደረጃጀት በአካባቢ ሰላምና ደህንነት ላይ የሰላም ሰራዊትን ማሳተፍ

ተግባር1:- የሰላም ሰራዊት በአካባቢ ሰላምና ደህንነት ውይይትና ጥበቃ ተሳታፊ ለማድረግ 12,000 ለማሳተፍ ታቅዶ 19,297 ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

## ግብ 9፡- የአካባቢን የደንብ ጥሰት የመከላከል አቅምን ማሳደግ

## ዓላማ1፡- የደንብ ጥሰቶችና አዋኪ ድርጊቶች ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማስደረግ

ተግባር1:- ህገ ወጥ ተግባራትን ሊያባብሱ የሚችሉ የደንብ ጥሰቶች 80 ታቅዶ 80 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

## ዓላማ 2፡- ጉዳት በደረሰባቸው መሰረተ ልማቶችን በመለየትማስተካከያ የማድረግ

ተግባር1:- ጉዳት የደረሰበት መሰረተ ልማት ለማሰተካከል 14 ታቅዶ 16 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ ፡

### ዓላማ 3፡- በህብረተሰብ የተሰሩ የውስጥ ለውስጥ የኮብል ስቶን መንገዶች ላይ ምልክትና ኬላዎችን እንዲተከሉ ማስደረግ፤

ተግባር 1፡- ከዋና አስፋልት ወደ ኮብል ስቶን የሚያስገቡ መንገዶች መግቢያ ላይ የትራፊክ ምልክቶች እንዲተከሉ 8 ታቅዶ 8 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር 2፡-  ከዋና አስፋልት ወደ ኮብል ስቶን የሚያስገቡ መንገዶች መግቢያ ላይ በኮብልስቶን በተሰሩ መንገዶች ላይ በተሽከርካሪዎች ጉዳት እንዳፈጸምባቸው 30 ኬላ

ለመትከል ታቅዶ 19 ተከናውናል፡፡ የዕቅዱን 63% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዘርፍ ሥራዎች ዕቅድ

## ግብ10፡- የኅብረተሰቡን የበጎፈቃድ አገልግሎት ባህል ማጎልበት

## ዓላማ1፡- የህብረተሰብ ክፍሎች በበጎፈቃድ አገልግሎት ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠርና ማስረጽ፤

ተግባር1፡- በበጎፈቃድ ፅንሰ ሃሳብ እና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ አመራር ዙሪያ ለ11,442 በጎፈቃደኞች፣ ባለድርሻ አካላትና የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 11,465 ግንዛቤ ለመፍጠር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር 2፡- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እና የማህበራዊ ኃላፊነት ደንብ ዙሪያ ለ1,890 የተለያዩ አካላት ግንዛቤ ለመፍጠርና ለማስተዋወቅ ታቅዶ አልተከናወነም፤

ተግባር3፡-በበጎፈቃድ አገልግሎት ዙሪያ 1 ኩነት (ቶክሾው፣ፓናል ውይይትና የፎቶ አውደ ርዕይ) መድረክ ለመፍጠር ታቅዶ 2 መድረኮች ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር4- በበጎፈቃድ አገልግሎት በተዘጋጁ ኩነቶች (ቶክሾው፣ፓናል ውይይትና የፎቶ አውደ ርዕይ) ላይ 890 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 900 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

### ዓላማ 2፡- 7 የበጎ ፈቃድ ማህበራትንና የት/ቤት ክበባትን መደገፍና ማጠናከር፤

ተግባር1፡- ለ14 በጎ ፈቃድ ማህበራት የግብዓትና የሙያ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 15 ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር2፡- በት/ቤቶች ለተቋቋሙ 20 የበጎ ፈቃድ ክበባት የሙያ ድጋፍ በማድረግ ለማጠናከር ታቅዶ 14 ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ የዕቅዱን 70% ማከናወን ተችሏል፡፡

ተግባር3፡- የበጎ ፍቃድ ማህበራት ጥምረት ለማጠናከር ፤

## ዓላማ 3፡- አሳታፊ የበጎፈቃድ መርሀ-ግብሮችን በመቅረፅ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ፤

ተግባር1፡- 88,736 በጎፈቃደኞችን በማሳተፍ 1,545,555 ችግኞችን ለመትከልና ለመንከባከብ ታቅዶ 136,547 በጎፈቃደኞችን በማሳተፍ 811,849 ችግኞችን መትከልና መንከባከብ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር2. በደም ልገሳ መርሃግብር 2,772 በጎፈቃደኞችን በማሳተፍ የደም ማሰባሰብ ተግባር ለማከናወን ታቅዶ 3,200 በጎፈቃደኞችን በማሳተፍ የደም ማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር3፡- በጎነት በሆስፒታል 99 በጎ ፈቃደኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 226 ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር4፡-21,008 በጎ ፈቃደኞች አካባቢን በማጽዳትና የጎርፍ ስጋትን በመከላከል ተግባራት ላይ በማሳተፍ 135 ሜ.ኪ ቆሻሻ እንዲወገድና 7 ሜ.ኪ የቦይ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮችን ጠረጋ ለማድረግ ታቅዶ 21,020 በጎ ፈቃደኞች በማሳተፍ 141 ሜኪ ቆሻሻ እንደወገድ ማድረግ ተችሏል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር5፡-በማዕድ ማጋራት ተግባር 5,042 በጎፈቃደኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 5,060 በጎ ፍቃደኞቸን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር6. በቤት እድሳት ተግባር 2,730 በጎ ፈቃደኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 2,741 በጎ ፍቃደኞቸን ማሳተፍ ተችሏል፡፡አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር7.በመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት 450 በጎ ፈቃደኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 660 በጎ ፍቃደኞቸን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር 8፡- «ሙያዬን ለሀገሬ» የሙያ በጎፈቃድ አገልግሎት ፕሮግራም 1,000 በጎ ፈቃደኛ የሆኑ የህክምና ባለሙያዎች፣ ኢንጅነሮች፣አርቲስቶች፣የህግ ባለሙያዎች፣መምህራን፤የመከላከያ አባላት፣የሃይማኖት መሪዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች … ወዘተ በሙያቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 970 አገልግሎት መስጠት ችለዋል፡፡ አፈጻጸሙን 97% ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር9፡-የአካባቢ ሠላም ማስጠበቅ እሴት ግንባታ ፕሮግራም ላይ 11,367 የሰላም ሠራዊት አባላት (በጎፈ ቃደኞች) ለማሳተፍ ታቅዶ 15,774 ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር10፡- በኪነ-ጥበብና መዝናኛ ፕሮግራም ላይ 20 በበጎፈቃደኛ ባለሙያዎች ተሳታፊ በማድረግ (በአጫጭርየትያትርናስነ-ፅሁፍ፣የጋዜጠኝነት፣የዘመናዊና ባህላዊ ውዝዋዜ፣ድምፅ) 1,400 የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲያሰለጥኑ ለማድረግ ታቅዶ 220 በበጎፈቃደኛ ባለሙያዎች ተሳታፊ በማድረግ 1,407 የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር11፡-የስፖርታዊ እንቅስቃሴ ፕሮግራም ላይ 25 አማተር ፕሮፌሽናል በጎፍቃደኛ የስፖርት አሰልጣኞችን በማሳተፍ 54,545 የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎችን በተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 25 አማተር ፕሮፌሽናል በጎፍቃደኛ የስፖርት አሰልጣኞች በማሳተፍ 55,200 የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር12፡-በከተማ ግብርና በመርሃ-ግብር ላይ 2,272 በበጎ ፈቃደኞች በማሳተፍ በመኖሪያ ቤቶች፣በትምህርት ቤቶችእና በወጣት ማዕከላት የተለያዩ ጓሮ አትክልቶች በማምረትእንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 2,294 በበጎ ፈቃደኞች ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር13፡-የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድጋፍ ፕሮግራም ላይ 527 በጎፈቃደኞችን በማሳተፍ የመንግስት ተቋማትን አገልግሎት ለደንበኞችና ለሰራተኞች ምቹና ሳቢ ለማድረግ ታቅዶ 545 ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር14፡-በወሰን የለሽ በጎፈቃድ መርሀ ግብር 220 በጎፈቃደኞች በተመረጡ ከተሞች በማሳተፍ የልምድ ልውውጥ ለማካሄድ ታቅዶ 285 ተሳትፈዋል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር15፡- 492 በጎ ፈቃደኞችን በቋሚነትና በመደበኛነት ለማሳተፍ ታቅዶ 500 በጎፍቃደኞች ማሳተፍ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችላል፡፡

## ዓላማ 4፡- የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላት የእውቅናና ሽልማት መስጠት፤

ተግባር1፡-በበጎፈቃድ አገልግሎት የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ 300 በጎፈቃደኞች፣ማህበራት፣መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትእና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን እውቅናና ሽልማት ለመስጠት ታቅዶ ለ300 የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላት የእውቅናና ሽልማትመስጠት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

## ግብ11፡-የበጎፈቃድ አገልግሎት ለዘላቂ ልማት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳደግ፡-

## ዓላማ1፡- በሚከናወኑ የሰው ተኮርና የበጎ ፈቃድ ተግባራት የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ፤

ተግባር 1፡- 332 ቤቶችን ለአቅመ ደካሞች፣ ለአረጋውያን፣ ለሀገር ባለውለታዎችና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ቤቶችን ለማደስና ለመገንባት ታቅዶ G+2 ከዚያ በላይ 352፣ በከፊል የታደሰ 110 እንዲሁም ሙሉ በሙሉ 38 አጠቃለይ 500 ቤቶች ማደስና መገንባት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር2፡- በሚታደሱና በሚገነቡ ቤቶች 1,654 ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 4,200 ቤተሰቦች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር3፡-75,021 ለሚሆኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ህብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ ለማጋራት ታቅዶ -----፤

ተግባር 4:- አንድ ቤተሰብ ለአንድ ሰው መርሀ ግብር 2,000 አቅመ ደካሞችን ከተለያዩ ድርጅቶች፣ የሀይማኖት ተቋማት፤ባለሀብቶች ወዘተ ጋር ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,700 አቅመ ደካሞችን ማስተሳሳር ተችላል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር5፡- 5,366 የህብረተሰብ ክፍሎች በበጎፈቃድ አገልግሎት በጤና መርሃ ግብሮች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 8,471 ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ተግባር6፡- 7,000 የሚሆኑ ተማሪዎችን በማጠናከሪያ ትምህርትና በክህሎት ስልጠና መርሃግብሮች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,210 ማከናወን ተችሏል፡፡የዕቅዱን 74.43% ማከናወን ተችሏል፡፡

ተግባር7፡- 8 በጎ ፈቃደኞችን በትምህርትና በስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ታቅዶ 8 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

## ዓላማ 2፡-በመንግስት ተደራሽ መሆን ያልቻሉ ተግባራትን የበጎፈቃድ አገልግሎት በማከናወን ሀብት መሸፈን፤

ተግባር1፡- በመንግስት ተደራሽ መሆን ያልቻሉ ተግባራትን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በማከናወን 504,201,682.4 ብር በሚገመት ሀብት እንዲሸፈን ለማድረግ ታቅዶ 938,970,670 ብር መሸፈን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን 100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

ከማዕድ ማጋራትና ትስስር ከተፈጠረላቸው አረጋውያንና አቅመ ደካሞች 170,195,690 ብር መሸፈን ተችሏል፡፡

- ቤት ከታደሰላቸው አረጋውያንና አቅመ ደካሞች እንዲሁም ሎውኮስት ቤት ግንባታ 956,559,100 ብር መሸፈን ተችሏል፡፡
- ስጦታዬ ለአዲስ አበባዬ መርሀግብር 3,075,860 ብር መሸፈን ተችሏል፡፡
- በደቡብ ክልል ጎፋ ዞን ለደረሰው የተፈጥሮአደጋ ድጋፍ 7,037,520 ብር መሸፈን ተችሏል፡፡ አጠቃላይ 938,970,670 ብር መሸፈን ተችሏል፡፡

# ክፍል አራት

## ምቹ ሁኔታዎች

- የክ/ከተማ አስተዳደሩ በብሎክ ለተፈጠረው አደረጃጀት ትኩረት የሰጠ መሆኑ እና ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ላይ የሚገኝ መሆኑ
- በክፍለ ከተማ እና በወረዳ የዘርፉ ሃላፊዎች የተሟሉ መሆናቸው
- በማህበረሰቡ ዘንድ ለአካባቢ ልማት ሰላም እና ጸጥታ እንዲሁም በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራዎች የተሻለ ተነሳሽነት መኖሩ
- የመንግስት አመራሩና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ መቻላቸዉ

## ጠንካራ ጎኖች

- በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከብሎክ እስከ ክ/ከተማ ያሉ አመራር እና ነዋሪዎች በተለያየ መድረክ ውይይት መካሄዱ
- በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በማጠናከሪያ ትምህርትና በክህሎት ስልጠና መርሃ ግብር ፣ቤተ እድሳት ፣ማዕድ ማጋራት ላይ ከዕቅድ በላይ መሰራቱ
- በህገወጥ መከላከልና ሰላም ማስፈን ዙሪያ ህብረተሰብ ከእቅድ በላይ በሻይ ቡና ውይይት ማድረግ መቻሉና አካባቢያቸውን በራሳቸው ተነሳሽነት በሮንድ መጠበቅ መቻላቸው
- የቅጥር ጥበቃ ደመወዝ የሚሰበሰበው በሀብት መሰብሰቢያ ደረሰኝ እየተሰበሰበ መሆኑና የቅጥር ጥበቃ ቀጥሮ የአካባቢን ሰላምና ፀጥታ መጠበቅ መቻሉ፡፡
- ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ የባለሙያ እጥረት ቢኖርም ባለው ውስን የሰው ሃይል ስራዎችን አቀናጅቶ መስራት መቻሉ
- በሰራተኛው ዘንድ እርስ በርስ የመደጋገፍ ባህል መኖሩ፤
- ለባለሙያዎችና ለበጎ ፈቃደኞች የአቅም ግንባታ መስጠት መቻሉ
- በየደረጃው የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መኖሩ

- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የትብብርና ቅንጅት ስርአት መዘርጋት መቻሉ

## የታዩ ክፍተቶች

- በተሰራጨው ደረሰኝ ልክ በጥሬ ገንዘብ ከመሰብሰብ አንጻር ውስንነት መኖሩ
- በተወሰኑ ወረዳዎች ላይ የተሰሩ ስራዎች ላይ መረጃ ጠምሮ መያዝ ላይ ክፍተት መኖሩ
- የሰራተኞች የክህሎት ችግር

# ያጋጠሙ ችግሮች

- ለመሰረተ ልማት ሀብት አሰባሰብ ተግባር በአመራሩ በኩል ትኩረት አለመስጠት
- በክፍለ ከተማም ሆነ በወረዳ ደረጃ የባለሙያ እጥረት መኖሩ
- የግብአት እና የበጀት ችግር በወረዳ ሰፊ ችግር ያለ መሆኑ
- ከእቅድ ውጪ በሚመጡ ደራሽ ስራዎች መጠመድ

## የተወሰዱ መፍትሄ እርምጃዎች

- የሀብት ማሰባሰብ ስራ በተሰራጨው ደረሰኝ ልክ እንዲሰበሰብ የግንዛቤ ስራ በመስራት
- የዘርፉ አመራሩ ከደራሽ ስራዎች ጎን ለጎን የጽ/ቤቱ ተግባር ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በድግግሞሽ በዘርፍ ላይ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ባለው ሰራተኛ ተግባራትን አቀናጅቶ መሰራቱና የባለሙያ ችግርን ለማቅለል በውስት እና በዝውውር በማምጣትና ውክልና በመስጠት ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደረጓል፡፡
- ከሌላ ጽ/ቤት የግብዓት ትብብር በመጠየቅ ስራዎችን ማከናወን
- መደበኛ ስራዎችን ከደራሽ ስራዎች ጋር አቀናጅቶ በመስራት
- በወረዳ ደረጃ ከዋና ስራ አስፈጻሚ ጋር በመነጋገር የፋይናንስ ድጋፍ እንዲደረግ በማድረግ
- ለመሰረተ ልማት ሃብት ማሰባሰብ ትኩረት እንዲሰጠው በዘርፍ የግንኙነት ግዜ በመገምገም ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ

## 4.1 የእቅድ አፈጻጸማችንን ተከትሎ የመጣ ለውጥ

- ❖ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ
- ❖ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ባለሀብቶች መኖራቸው
- ❖ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል አደረጃጀት መፈጠሩ
- ❖ በብሎክ ደረጃ በርካታ ተሳትፎ መደረግ መቻሉ

## 4.2. ከ100% በላይ እና ከ50% በታች ያሳዩ አፈጻጸሞች ምክንያት

- ➢ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባራቶች አብዛኞቹ አፈጻፀማቸው100% በላይ ነው ምክንያቱም በየደረጃው ትኩረት ተሰጥቶት የተግባሩ አፈጻፀም የሚገመገም መሆኑ

- ➢ የኮብልስቶን ጥገና 50% በታች የሆነበት ምክንያት የጥገና ስራ በመንገድ ባለስልጣን ጽ/ቤት በሶስተኛው ሩብ ዓመት ለማከናወን እቅድ የተያዘ በመሆኑ ነው፡፡
- ➢ ከመሰረተ ልማት ስራዎች አኳያ ከ100% በላይ የተከናወኑ ተግባራት ምክንያት አብዛኖቹ የልማት ስራዎች ከህብረተሰቡ በተሰበሰበ ገንዘብ እና በስፖንሰር በመከናወናቸው ነው

### 4.3. ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

- ➢ የሰው ተኮር ፕሮጀክት ስራዎችን በማጠናከር የክፍለ ከተማችን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ
- ➢ በየወረዳው በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተጠቃሚ ልየታ ላይ በአግባቡ በመስፈርቱ መሰረት ልየታውን በማካሄድ ተጠቃሚ ማድረግ
- ➢ ለመሰረተ ልማት ግንባታ አገልግሎት የሚውል ሀብት ማሰባሰብ በተሰራጨው ደረሰኝ ልክ አጠናክሮ ማስቀጠል
- ➢ የሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ብሎክ ካውንስሎችን ያሳተፈ በፀጥታ ዙሪያ ንቅናቄ ማካሄድ
- ➢ ለአመራርና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና በተከታታይ መስጠት
- ➢ ከአጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

## ማጠቃለያ

የልደታ ክፍለ ከተማ ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በአራት የስራ ሂደቶች የተዋቀረ ሲሆን በመሰረት ልማት በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢ ልማት ስራዎች ሲሰማራ፣ ህገ ወጥ መከላከልና ሰላም ማስፈን ዘርፍ የክፈለ ከተማችን ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ሰላም እና ጸጥታ እንዲያሥከብሩ ህገ ወጦችን በመከላከል ሰላማቸው ሰፍኖ መብታቸውን አስከብረው በልማት እና ዲሞክራሲ ስርዓት ላይ ርብርብ በማድረግ ሁለንተናዊ ስኬቶችን በማረጋገጥ ሰላሙና ደህንነቱ የተጠበቀ ትውልድ መፍጠር እና መቅረጽ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ በመሆኑ፡ እንዲሁም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ህብረተሰቡ ወይም በጎ ፈቃደኞች በክፍለ ከተማ ዉስጥ የሚታዩትን ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሳተፉበት እና የነዋሪዉን ችግር ከመቅረፍ ረገድ የላቀ ሚና መጫወቱ ዋነኛዉና እና ሊተኮሩበት የሚገባ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከአጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በመተግበር እና የዜጎችን የሰላምና ደህንነት እንዲሁም የልማት ስራዎችን ማጠናከር ቀዳሚ አጀንዳ በማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ጽ/ቤቱ አራቱንም ዘርፎች በማቀናጀት በክፍለ ከተማችን የተጀመረውን የእድገት ጉዞ ቀጣይነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ የመሰረተ ልማት፣የሀብት አሰባሰብ ፕሮጀክት ዝግጅትና ግምገማ ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ የሰላምና ጸጥታ ስራ እንዲሁም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ የህዝቡን ተሳታፊነት፣ ባለቤትነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ቁልፍ ማጠንጠኛ ያደረገ የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ነው፡፡

